# የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ

አባይነህ አስማረ

03-09-15

ከመላው የትግራይ ህዝብ ማንነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ወያንነት በተነሳ ቁጥር መቐለም አብራ መነሳቷ ግድ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ለህ.ወ.ሐ.ት የትጥቅ ትግል ፅኑ መሰረት ጥሎ እንዳለፈ የሚነገርለት የቀዳማዊ ወያነ ፀረ ብሔራዊ ጭቆና የአመፅ ንቅናቄ ማዕከሉን እዚህችው መቐለ ላይ አድርጐ ነበርና ነው ከአጼ ሃይለ ስላሴ የአገዛዝ ስርአት ጋር የተፋለመው።

እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መቐለን በገዢ መደቦች አፈና ምክንያት ተዳፍሮ የቆየው ለትግራይ ህዝብ መብትና ነፃነት የመታገል መንፈስ ተለይቷት አያውቅም ቢባል ከእውነታው መራቅ አይሆንም። ለዚህም አሁን 40ኛ ዓመቱን እያከበረ የሚገኘው ህ.ወ.ሓ.ት በ1967 ዓ.ም የየካቲት 11 ቀን እንዲመሰረትና ከሰላሳ ሁለት ዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ተዳፍኖ የቆየውን የብሔራዊ ጭቆና ትግል፣ ወይም የወያነ ትግራይ ዳግማዊ ንቅናቄ እንዲቀጣጠል በማድረግ ረገድ የመሪ ተዋናይነትን ሚና የተጫወቱት የክልሉ ተወላጆች፣ እዚሁ መቐለ ውስጥ በህቡዕ እየተገናኙ ይመክሩ እንደነበር ማስታወስ ይቻላል።

ሌላው በዚህ አጋጣሚ ሳናወሳው ማለፍ የማይኖርብን ጉዳይ ደግሞ፣ ከዛሬ አርባ አመት በፊት ህ.ወ.ሓ.ትን ደደቢት ላይ የመሰረቱት ወጣት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ ቀዳማዊ ወያነ በመባል የሚታወቀው የትግራይ አርሶ አደሮች፣ የፀረ ብሔራዊ ጭቆና ንቅናቄ በ1935 ዓ.ም የተካሔደበትን አግባብ ወይም የንቅናቄውን ፍትሐዊነት በሚመለከት የማያሻማ አቋም ይዘው የተነሱ መሆናቸውን ነው።

ማለትም የህ.ወ.ሓ.ት መስራች አባላት ገና ከመነሻው ጀምሮ "የቀዳማዊ ወያነ ጥያቄም ሆነ ንቅናቄው መላው የትግራይ ህዝብ በገዢ መደቦች የሚፈፀምበት ብሔራዊ አድሎና መገለል እንዳንገሸገሸው የሚያመላክት ነባራዊ እውነታ እንጂ፣ የአንድ አካባቢ (የተወሰነ ህብረተሰብ) ያነሳው ተራ ቅሬታ ተደርጐ መወሰድ የለበትም" የሚል ፅኑ አቋም እንደነበራቸው ይታወቃል። የቀዳማዊ ወያነ ፀረ ብሔራዊ ጭቆና የነፃነት እንቅስቃሴ ይዞት የተነሳውን ፍትሐዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ውጤት ሳያመጣ የቀረውም፣ ዕውቀት ላይ በተመሠረተ ንድፈ ሃሳባዊ ትንተና ብቁ አመራር የሚሰጥ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት ስላልነበረው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም የሚል ፅኑ እምነት አለው - ህ.ወ.ሐ.ት።

ከዚሁ ፅኑ እምነቱ በመነጨ የፀረ-ብሔራዊ ጭቆና ትግል ዙሪያ መላውን የትግራይ ህዝብ አሰልፎ ለመፋለም ያለመ የፖለቲካ ፕሮግራም ይዞ በመነሳቱም ነበር ህ.ወ.ሓ.ት የገጠሙትን ውስብስብ ፈተናዎች ሁሉ ተጋፍጦ እያለፈ

ወርቃማውን ታሪክ ለመፃፍ የበቃው። እንግዲያውስ የዚህ ፅሁፍ ዋነኛ ትኩረት የሆነችው መቐለም ከመቼውም ጊዜ በላይ ውበት ድምቀት ተጐናፅፋ መሰንበቷም ያለምክንያት አይደለም።

ይልቁንስ ከዚሁ እምነቱ በመነጨ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት የተመሰረተው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ /ሕ.ወ.ሓ.ት/ ለቀዳማዊ ወያነ ውድቀት ወይም ሽንፈት ምክንያት ናቸው ያላቸውን ታሪካዊ እውነታዎች ባገናዘበ መልኩ፤ የተመሰረተበትን አርባኛ አመት ለማክበር ሽር ጉድ እያለች የከረመችው መቐለ በአሉን ያስተናገደችበት ድባብ ምን ያህል ድምቀት የተላበሰ እንደነበር ልንገራችሁ።

ይልቁንስ ብሔራዊ አድሎና መገለል ክፉኛ ያስመረረው የትግራይ ህዝብ፤ በመሪ ድርጅቱ በህ.ወ.ሐ.ት ጥላ ስር ተደራጅቶ፤ ያካሔደው የትጥቅ ትግል የተጀመረበትን 40ኛ አመት ለማክበር፤ ከመላው የሀገራችን ክፍልና እንዲሁም ከዓለም ዙሪያ ጭምር የመጡ እንግዶቿን ለመቀበል እንጂ። ስለዚህ መቐለ በእርግጥም የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሰሜናዊት ኮከብ የመሆኗን እውነታ እመሰክር ዘንድ ተገቢ ነውና ብዕሬን አንስቻለሁ።

"ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል" እንዲሉም ይህች የትግራይ ብሔራዊ ክልል ርዕሰ ከተማ መቐለ ሰሞኑን ምን ያህል አምሮባት እንደሰነበተች፤ ከብዙ በጥቂቱ ላውጋችሁ ፈልጌ የጀመርኩትን ጨዋታ በክፍል ሁለት ፅሁፌ እንደምጨርስላችሁ ቃል ልግባና የዛሬውን እዚህ ላይ ላብቃ። ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሳንወጣ ሌላም ጠቃሚ ሃሳቦችን እያነሳን መጨዋወታችን እንደምንቀጥልም ተስፋ አድርጋለሁ።

በዚሁ ርዕስ የቀረበውን ክፍል አንድ ፅሁፌን ያነበባችሁ እንደምታስታውሱት፤ ባለፈው የካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም የተከበረውን የህ.ወ.ሐ.ት 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ያስተናገደችው መቐለ ከተማ ምን ያህል አምሮባት እንደሰነበተች የሚያወሳ ምስክርነቴን ለመግለፅ ሞክሪአለሁ፡፡ ያኔ የጀመርነውን በመቐለ ክራሞት ዙሪያ የሚያጠነጥን ወጋችንን ካቆምንበት ለመቀጠል ቀጠሮ ይዘን እንደነበርም አይዘነጋም፡፡

እንግዲያውስ በቀጠሮአችን መሰረት መቐለ የሰነበተችበትን እውነታ ከሞላ ጎደል የሚያስቃኝ ክፍል ሁለት ፅሁፌን እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁና አብረን እንቆይ፡፡ አሁን የምንገኘው የትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግስት መቀመጫና እንዲሁም የህ.ወ.ሐ.ት ዋና ጽህፈ ቤት ማዕከል በሆችው የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሰሜናዊት ኮከብ ከተማ ውስጥ ነው፡፡፡...

"ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል" እንዲሉ አበው እነሆ መቐለን ከእግር እስከ ራሷ መቃኘት ይዘናል፡፡ በተለይም የበዓሉን ዝግጅት በቀጥታ ከስፍራው የማስተላለፍ ታሪካዊ ሃላፊነት የወሰዱት የፕሮድካስቲንግ መገናኛ ብዙሃኖቻችን ቀዳሚ ትኩረት ከነበረው ክንውን ትንሽ ወጣ ብለን የታዘብነውን የትግራይ ሕዝብ ታጋይነት ጎልቶ የሚገለፅበት እውነታ ሳናካፍላችሁ እናልፍ ዘንድ ፈፅሞ ህሊናችን አይፈቅድልንምና እርሱን እናስቀድም፡፡

ካለፈው የካቲት 6 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እንደ እኔ መቐለ ከተማ ውስጥ የመገኘት እድል የገጠመው ማንኛውም ሰው ሊመሰክር የሚችለው አንድ ጉልህ ሀቅ ቢኖር፤ ህ.ወ.ሐ.ት መራሹ የትጥቅ ትግል የማይመለከተው አንድም እንኳን የትግራይ ምድር ተወላጅ እንደሌለ ነው፡፡

ለዚህ ታሪካዊ የትግራይ ሕዝብ የጋራ እውነት ጥሩ ማረጋገጫ ሊሆነን የሚችለው ደግሞ ምን መሰላችሁ ? የክልሉ ርዕሰ ከተማ መቐለ ሰሞኑን በከፍተኛ ድምቀት ያስተናገደችውን የድርጅቱ አርባኛ ዓመት የምስረታ በዓል ሕዝቡ ራሱ ልክ እንደ አንድ ትልቅ ብሔራዊ ርዕሰ ጉዳይ ሲቆጥረው መስተዋሉ ነው፡፡

ለምሳሌ ያህልም እኔና አብረውኝ የሄዱት የሥራ ባልደረቦቼ መቐለ ውስጥ በቆየንባቸው ቀናት፤ ነዋሪው ሕዝብ የበዓሉን ድምቀት ይበልጥ ለማጉላት ያለመፈረጇ ብዙ ጥረት ሲያደርግ እንደነበር ታዝበናል፡፡ ከዚህም ባሻገር እያንዳንዱ ሰው የበዓሉን አጠቃላይ ድባብ በፍፁም የባለቤትነት ስሜት ከመከታተል እንዳልቦዘነ የሚያመለክት ታሪካዊ ገጽታ ተላብሳ ነው የሰነበተችው መቐለ ከተማ፡፡

በተለይም ደግሞ ለድፍን 17 ዓመታት በተካሄደው ፀረ ብሔራዊና መደባዊ ጭቆና የትጥቅ ትግል ክቡር ህይወታቸውን ካጡት ስድሳ ሺህ ሰማዕታት መካከል፤ የአርባዎቹ ቅሪተ-አካል ወይም አፅም ከየተቀበሩበት የትግራይ ምድር ጫካ ውስጥ እየተለቀመ እንዲመጣ መደረጉን የሰሙ አንዳንድ የመቐለ ነዋሪዎች ደስታቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው ማየቴ አስገርሞኛል፡፡

የአርባዎቹን ሰማዕታት የህ.ወ.ሐ.ት ታጋዮች አፅም የያዘው የሬሳ ሳጥን ወደ መቐለ ሲገባ የከተማዋ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ እልልታውን እያቀለጠው እንደነበርና እጅግ በጣም የሞቀ አቀባበል እንደተደረገለትም ለመታዘብ በቅተናል፡፡

ሌላው በመቐለ ቆይታችን ህ.ወ.ሐ.ት መራሹ የትጥቅ ትግልና መላው የትግራይ ሕዝብ ምን ያህል ጥብቅ ቁርኝት እንደነበራቸው የተገነዘብንበት ጉዳይ ከተማዋ ውስጥ የሚገኙ በርካታ የግል ንግድ ድርጅቶች ጭምር "እንኳዕን መል 40 ዓመት ምጅማር ብረታዊ ቃልሲ ሕዝቢ ትግራይ አብፅሀና አብፅሀጁም" (እንኳን የትግራ ሕዝብ የትጥቅ ትግል ለተጀመረበት 40ኛ ዓመት አደረሰን አደረሳችሁ) የሚል ፅሁፍ በየበራቸው ሰቅለው ማየታችን ነው፡፡

እንዲሁም በትጥቅ ትግሉ ዘመን የህ.ወ.ሐ.ት ታጋይ አርቲስቶች የዜማቸው ወኔ ቀስቃሽ የትግርኛ ዘፈኛች ጎላ ብለው የማይደመጡበት አንድም ቤት መቐለ ውስጥ አልነበረም ብንል ማጋነን አይሆንብንም፡፡ ሶስት ኤርትራውያን ታዋቂ አርቲስቶችን ጨምሮ፤ በርካታ የትግርኛ ዘፋኞች የተሳተፉበት የሙዚቃ ድግስ "ሮማናት" እየተባለ በሚጠራው አደባባይ ለተከታታይ ቀናት የቀረበበትን ደማቅ ዝግጅት ለመመልከት ከየቤቱ የሚወጣው የመቐለ ከተማ ነዋሪ ቁጥር እጅግ የሚያስገርም እንደነበረም ተመልክተናል፡፡

በተለይም የሀገራቸው ፈላጭ ቆራጭ መንግስት በህዝቡ ላይ የሚፈፅመውን መጠነ ሰፊ በደል ተቃውመው ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱት ሶስት ኤርትራውያን ወጣት አርቲስቶች፤ አደባባዩ መሀል ወደ ተዘጋጀው ተንቀሳቃሽ መድረክ

በወጡ ቁጥር የሙዚቃ ድግሱ ታዳሚ ከነበረው ሕዝብ ዘንድ የሚቸራቸው አድናቆት ጭብጨባ አስገራሚ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ እነርሱም ግን ለመላው የመቐለ ከተማ ነዋሪ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ለትግራይ ሕዝብ ያላቸውን አክብሮት ከልብ በመነጨ የወንድማማችነት መንፈስ ከመግለፅ እንዳልተቆጠቡ ነው ያስተዋልኩት፡፡

ለአብነት ርዕሶም የሚባለው ድምፃሚ "ኢታዓባይ ነፋሪት" በተሰኘ ተወዳጅ ዜማው፣ መቐለና አስመራ ፈፅሞ ሊነጣተሉ የማይችሉ አህትማማች ከተሞች ስለመሆናቸው የሚያወሳ እጅግ በጣም ጠቃሚ መልዕክት ያስተላልፍ እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡

"በዓለማችን የትግርኛ ቋንቋን የምንናገረው እኛና እናንተ ብቻ ሆነን ሳለ፣ ታዲያ እንዴት ልንለያይ እንችላለን!?" ሲል ታዳሚውን የጠየቀው ርዕሶም፣ ሀገሩ ኤርትራ አሁን ካለችበት አሳዛኝ እውነታ የምትወጣበት ቀን እሩቅ እንደማይሆንና ያኔ ደግሞ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ሕዝቦች እርቅ አውርደው፣ ቂም አብርደው በመልካም ጉርብትና ላይ የተመሰረተ ወንድማማችነታቸውን የማያድሱበት ምክንያት እንደማይኖር ያለውን ተስፋ ሲገልፅ ተደጧል፡፡

እንግዲህ መቐለ በህ.ወ.ሐ.ት 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ዋዜማ የነበረችበት አጠቃላይ ሁኔታ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል ፡፡ በግልፅ አነጋገር የትግራይ ህዝብ ከቀዳማዊ ወያነ ንቅናቄ ጀምሮ፣ ለብሔራዊ መብቱና ነፃነቱ መከበር ያካሄደውን ፀረ-ጭቆና ተጋድሎ፣ እንዲሁም ተጋድሎው የጠየቀውን ፈርጀ ብዙ መስዋዕነትነት አጉልተው በሚያንፀባርቁ ታሪካዊና ነባራዊ እውነታዎች ያሸበረቀ የሕዳሴ መንፈስ ተላብሳለች ማለት ይቻላል፡፡

ህ.ወ.ሐ.ት መራሹን ፀረ-ጭቆና የትጥቅ ትግል በድል አድራጊነት ለመወጣት ሲባል፣ መላው የትግራይ ሕዝብ ያሳየው ቁርጠኝነትና የከፈለው መጠነ ሰፊ መስዋዕትነት፣ መና እንዳልቀረም ጭምር ነው የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ ከተማ መቐለ የምታረጋግጥልን፡፡

ለዚህ አባባሌ ዋቢ መጥቀስ ካለብኝ ደግሞ፣ የህ.ወ.ሐ.ትን 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ምክንያት በማድረግ እዚያው መቐለ ውስጥ ተዘጋጅቶ የነበረው ባዛር ላይ፣ በተለያየ መስክ ተሰማርተው ትግራይን በማልማት ረገድ የየበኩላቸውን ድርሻ እየተወጡ የሚገኙ በርካታ የክልሉ ተወላጅ ባለሀብቶች ይዘውት የቀረቡት ልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ምርት ብቻ ጥሩ ምሳሌ ይሆነኛል ባይ ነኝ፡፡

ምክንያቱም "ዓዲሃቂ" ተብሎ በሚጠራው የከተማዋ ክፍል በሚገኘው የሰማዕታት ሐውልት ቅጥር ጊቢ ውስጥ በተዘጋጀውና ለድፍን አንድ ወር ክፍት ሆኖ እንዲቆይ በተነገረለት ባዛርና የንግድ ትርኢት ላይ ያልቀረበ የምርት ዓይነት አልነበረምና ነው፡፡

በተረፈ ግን የካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊባል በሚችል ድምቀት ስለተከበረው የህ.ወ.ሐ.ት አርባኛ ዓመት የምስረታ በዓል አጠቃላይ ድባብ ይህን ሲመስል ይህንን ልማት ሰላምና ዴሞክራሲ እንዳያብብና ህዝባችን ከድህነት ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዳይሆን የሚንቀሳቀሱ ወገኖች መኖራቸው ግን አይካድም።

ከእነዚህም መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ሽብርተኝነትና ጽንፈኝነት ነው። ሽብርተኝነትን መታገል የመላው ሰብዓዊ ፍጡር አንገብጋቢ ጉዳይ ስለመሆኑ አለም ከተስማማበት ቆይቷል፡፡

እናም በዚሁ አለም አቀፋዊ ስምምነት መሠረት አደጋውን ለመመከት አበክረው ከተንቀሳቀሱ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ የመሆኗ ጉዳይ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሽብርተኝነት የሚያስከትለውን ፈርጀ ብዙ ጥፋት በመገንዘብ ረገድ ግንባር ቀደም የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ አደጋውን ለመከላከልና ብሎም ለማስቀረት ይቻል ዘንድ ያላሰለሰ ጥረት ስታደርግ መቆየቷም የሚታወቅ ነው፡፡

ከዚህ አኳያም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት ላሳየው ቁርጠኛ አቋምና ሀገራችን በምታካሂደው ጠንካራ የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል ላስመዘገበችው አመርቂ ውጤት በርካታ የአለም መሪዎች ጨምር አድናቆታቸውን ሲቸሩን ተስተውለዋል፡፡

በእርግጥም ደግሞ በኤርትራው መንግስት ፈርጀ ብዙ ድጋፍ እየታገዙ መላውን የአፍሪካ ቀንድ ለማተራመስ የሚንቀሳቀሱት፤ እንደአልሼባብ ዓይነቶቹ ሽብርተኛ ቡድኖች፤ በተለይም ኢትዮጵያ ያሳይ ያነጣጠረ ጥቃት ለመፈፀም የማይፈነቅሉት ድንጋይ ያለ መኖሩን ያህል ተደጋጋሚ ሙከራቸው እምብዛም ሲሳካ የማይስተዋለው ያለምክንያት አይደለም፡፡

ይልቁንስ በሰላማዊ ህዝብ ላይ የሚፈፀም የሽብርተኞች ጥቃት የሚያስከትለውን መጠነ ሰፊ ጥፋት አበክሮ የተገነዘበው የኢፌዲሪ መንግስት፤ የዜጎቹን ህይወትና ንብረት ከአደጋው ለመጠበቅ ሲል ባወጣው የሕግ ማዕቀፍ መሰረት፤ የምናካሂደው ሀገር አቅፋዊ የፀረ ሽብርተኝነት ትግል አላላውስ ስላላቸው እንጂ፡፡

ለዚህ ደግሞ በተለይም የሶማሊያው አልሸባብና የጥፋት አጋሮቹ ለዚህ አገር ህዝቦች የሚደግሱልን የሽብር ጥቃት ሴራ ሁሉ፤ ገና በውጥኑ መክኖ እንዲቀር የተደረገባቸውን እጅግ በርካታ የፀረ ሽብር ትግሉ አመርቂ ውጤቶችን ማስታወስ ይቻላል፡፡

የዛሬዋ ኢትዮጵያ በአስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ውስጥ የመገኘቷ መሰረታዊ ምክንያት ይህ ሆኖ ሳለ ግን፤ አንዳንድ አመፅ የመናፈቅ አባዜ የተጠናወታቸው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነባራዊ እውነታውን ለማምታታት ሲሞክሩ ይስተዋላሉ፡፡

ለአብነት ያህልም አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ ላይ የሚያሰማውን ያልተገባ ተቃውሞ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህ ፓርቲ የፀረ ሽብር ሕጉን አስፈላጊነት የማያምን ከመሆኑም ባሻገር፤ ሕጉን ለማሰረዝ ያለመ የፊርማ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መሰንበቱ የሚታወስ ነው፡፡

ለነገሩ ሌሎቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ፤ የፀረ ሽብርተንነት ሕጉን ፋይዳ በቅጡ ካለመረዳት የሚመነጭ የሚመስል ቅሬታቸውን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲገልፁ ይደመጣሉ፡፡

ስለዚህ የዘንድሮ ጠቅላላ ምርጫ ላይ እነርሱ አሸንፈው ይህችን ሀገር የመምራት እድል ቢገጥማቸው፤ ሽብርተኝነትን በመታገል ረገድ ሊኖራቸው የሚችለው አቋም ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ከወዲሁ መነሳት ያለበት ሆኖ ይሰማኛል፡፡

ምክንያቱም አሁን በምንገኝበት አለም አቀፋዊ እውነታ ውስጥ ከሁሉም ነገር በፊትና በላይ መሟላት የሚኖርበት እጅግ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ፤ አስተማማን ሰላምና መረጋጋት የማስፈን ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል ነው፡፡

በተለይም ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ከፈርጀ ብዙ ድህነትና ኋላ ቀርነት ጋር የሞት ሽረት ትግል ለገጠመች ሀገር፤ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋጥ የማስፈን ወይም ያለ ማስፈን ጥያቄ የህልውና ጉዳይ ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡

ስለሆነም ለአምስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የሚደረገው የምረጡኝ ቅስቀሳ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምታካሂደው የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል አኳያ በተቃኘ መልኩ መቅረብና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ረገድ የሚያራምዱትን የተዛባ አቋም መራጩ ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ይጠበቅበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በገልፅ አነጋገር፤ መላው የሀገራችን ሕዝቦች ስር የሰደደ እንዲሁም ድህነትና ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ ሲሉ፤ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚያካሂዱትን ዘርፈ ብዙ የህዳሴ ጉዞ፤ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የመቀልበስ አላማ ያቸው ሃይሎች፤ ሰላማችንን ለማደፍረስና እንዲሁም ልማታችንን ለማፍረስ ቢሞክሩ ፈፅሞ ልንፈቅድላቸው እንደማይገባ እንደ ሀብረተሰብ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ይጠበቅብናል ማለቴ ነው፡፡

መቼም አሁን በሀገራችን የሚስተዋለው አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ባይኖር ኖሮ፤ እያንዳንዱ ዜጋ ያለምንም ስጋት እየተንቀሳቀሰ ሀብት ንብረት ለማፍራትም ሆነ እንደልቡ ለመማር አይችልም ነበር አይደል?

ስለዚህም የዘንድሮውን ጠቅላላ ምርጫ ምክንያት በማድረግ፤ ኢትዮጵያውያንን እርስ በእርስ የሚያናቁር የአመፅ ተግባር ለመቀስቀስ የሚሹ የፖለቲካ ኃይሎች፤ በመብታችን ከመቀለድ እዲቆጠቡ አበክረን እናስገነዝባቸው ዘንድ ግድ ይሆናል፡፡

ደግሞስ እነዚህ አመፅ ናፋቂ ኃይሎች በመብታችን ሲቀልዱ በቸልታ የምንመለከታቸው እስከ መቼ ነው? እንደ እኔ እምነት ከሆነ ሕብረተሰቡን እንደ አላዋቂ ከመቁጠር በመነጨ መታበይ ይህችን ሀገር ሊያምሷት የሚሞክሩ ተቃዋሚ

ፓርቲዎች፤ መላው ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች በዘመናት ትግላቸው ለተቀዳጁት ሕገ-መንግስታዊ መብትና ነፃነት፤ ተገቢ ክብር እንዲሰጡ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡

አለበለዚያ ግን፤ እነዚሁ ነውጥ የመናፈቅ አባዜ የተጠናወታቸው የፖለቲካ ኃይሎች፤" በመጭው ግንቦት ወር 2007 ዓ.ም የሚካሄውን ጠቅላላ ምርጫ፤ ወደለየለት አመፅና ብጥብጥ በመቀየር ስርዓቱን መናድ ይቻላል" የሚል እምነት ይዘው ስለተነሱ፤ የጥፋት አጀንዳቸውን ለማሳካት የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደማይኖር መገመት አያዳግም፡፡

ለምሳሌ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍተህ እንዲሁም ሰማያዊ ፓርቲ፤ አምስተኛውን እምነት፤ ያንኑ ለማድረግ ያለመ ግልፅና ስውር እንቅስቃሴ ሲያካሂዱ ከቆዩ ተቃዋሚ ሃይች ዋነኞቹ ስለመሆናቸው ተወርቶ ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡

እነዚሁ ሃይሎች፤ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን አምርረው ከመቃወምና " ይሰርዝልን" እያሉ ከመወትወት ቦዝነው የማያውቁትም፤ ሕጉ የአመፅ ተግባር ለማከናወን የማያመች ሆኖ ስላገኙት እንጂ ሌላ መሰረታዊ ምክንያት ኖሯቸው አይደለም፡፡ ይሄው አሁን ደግሞ ተልካሻ ሰበብ አስባብ እየፈጠሩ፤ በዘንድሮው ምርጫ ላለመሳተፍ መወሰናቸውን በመግለፅ ላይ ነው የሚገኙት፡፡

በሀገር ውስጥ "የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ..." የተናገሩ ግን ደግሞ የምርጫ ሂደት ውስጥ መግባትን እንደ "ከንቱ ልፋት" ከሚቆጥሩት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ የሆነው መ.ኢ.አ.ድ. ራሱ፤ የአመፅ ሴራውን በመዶለት ረገድ እንቅልፍ አጥቶ ማደር ከጀመረ ሰንባብቷል ነው የሚባለው፡፡

ስለዚህም ሀገራችንና መላው ህዝቦቿ ከአሳፋሪው የተመፅዋችነት ታሪክ መጥተው ለማየት የምንሻ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ሁሉ፤ ጉዳዩን በአንክሮ እናጤነው ዘንድ ተገቢ ሆኖ ይሰማኛል፡፡